# ሰብአዊ መብቶችን እንደ መሟገቻ መሳሪያ መጠቀም

በትብብር የተዘጋጀ፡-

HUMAN RIGHTS

room to heal

# Contents


2 የሰብአዊ መብቶች ኣዋጅ ምንድን ነው እናም እንዴት ነው የሚሰራው?

4 በሰብአዊ መብቶች ኣዋጅ ውስጥ ምን መብቶች አሉ?

5 ፍፁም እና ፍፁም ያልሆኑ መብቶች

6 አንቀፅ 3፡- ከኢሰብአዊ እንዲሁም አዋራጅ ከሆነ አያያዝ ነጻ የመሆን መብት

7 አንቀጽ 8፡- የግል እና የቤተሰብ ህይወት፣ የቤት እና የመልእክት ልውውጥ መብት

9 አንቀጽ 14፡- ከአድልዎ ነፃ የመሆን መብት

11 ሰብአዊ መብቶች በሙግት፡- ደብዳቤ አጻጻፍ

15 ሰብአዊ መብቶች በሙግት፡- ምላሽዎን ከፍ ማድረግ

17 ሰብአዊ መብቶች በሙግት፡- መዝግቦ ማስቀመጥ

# የሰብአዊ መብቶች ኣዋጅ ምንድን ነው እናም እንዴት ነው የሚሰራው?

## የሰብአዊ መብቶች ኣዋጅ

ሰብአዊ መብቶች በመንግስት፣ የህዝብ አገልግሎቶች እና ሰራተኞቻቸውን ጨምሮ እንዴት መስተናገድ እንዳለብን የሚገልጽ የመመሪያ መጽሐፍ ነው። ሰብአዊ መብቶች ከእሴቶች በላይ ናቸው፣ ሰብአዊ መብቶችን በህግ በመጠበቅ። በእንግሊዝ ውስጥ ይህ ህግ የሰብአዊ መብቶች ኣዋጅ ይባላል። በሰብአዊ መብቶች ኣዋጅ ላይ ተጨማሪ መረጃን እዚህ ማግኘት ይችላሉ።

ሰብአዊ መብቶች እንዲከበሩ መጠየቅ የተለየ አይነት መስተንግዶን መጠየቅ አይደለም። ህጉ እንዲከበር መጠየቅ ነው።

## በሰብአዊ መብቶች ኣዋጅስር መብት ያለው ማነው?

በእንግሊዝ ውስጥ የሚኖር ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ መብቶች አሉት። 'ሁለንተናዊ' ናቸው ይህም ማለት ለሁሉም ናቸው ማለት ነው – ማንም ይሁን ማን። የትም አይነት ቦታ ቢወለዱም እንኳን፣ በእንግሊዝ ውስጥ ከሆኑ የሰብአዊ መብቶችዎ በሰብአዊ መብቶች ኣዋጅ     መሰረት ይጠበቃሉ። የስደት ሁኔታዎ ምንም ይሁን ምን ለውጥ አይኖረውም።

## የሰብአዊ መብቶች ኣዋጅን መቼ መጠቀም እንችላለን?

የሰብአዊ መብቶች ኣዋጅ ለህዝብ ባለስልጣናት እና ህዝባዊ ተግባራትን ለሚያከናውኑ አካላት ተፈጻሚ ይሆናል። ይህም ማለት አንድ የግል ኩባንያ ህዝባዊ ተግባራትን እያከናወነ ከሆነ በሰብአዊ መብቶች ህግ መሰረት ግዴታዎች ይኖሩባቸዋል። በእነዚህ አካላት ውስት በሁሉም ደረጃ ላይ የሚሰሩ ሰራተኞችን ይመለከታል።

የሰብአዊ መብቶች ኣዋጅ ክፍል 6 በሁሉም የመንግስት ባለስልጣናት እና በእነሱ ውስጥ የሚሰሩ ሰራተኞች ህጋዊ ግዴታን ያስቀምጣል። በየእለቱ በሁሉም ስራዎቻቸው ከሰብአዊ መብቶች ጋር በስምምነት መስራት ይኖርባቸዋል። ይህም ማለት የሰብአዊ መብቶች ኣዋጅ የመንግስት ባለስልጣናት በድርጊቶቻቸው፣ በውሳኔዎቻቸው፣ በፖሊሲዎቻቸው እና በአገልግሎቶቻቸው ሰብአዊ መብቶችን እንዲያከብሩ፣ እንዲጠብቁ እና እንዲያሟሉ ህጋዊ ግዴታን ይጥላል።

## በሕዝብ አካላት ላይ ያለው ግዴታ

ምንም እንኳን አንዳንድ መብቶች ሊገደቡ ቢችሉም፣ የማክበር ግዴታ ማለት የመንግስት ባለስልጣናት መብቶችዎን ሊነፍጓቹ አይገባም ማለት ነው። የመጠበቅ ግዴታው 'ጥበቃ ማድረግ (Safeguarding)' በመባልም ይታወቃል። ይህም ማለት የመንግስት ባለስልጣናት መብቶችዎ አደጋ ላይ መሆናቸውን ከተረዱ እርስዎን ለመጠበቅ ጣልቃ መግባት ይኖርባቸዋል ማለት ነው። የማሟላት ግዴታ ማለት በሰብአዊ መብቶችዎ ላይ የሆነ ችግር ሲፈጠር መንግስት ምርመራ ማድረግ ይኖርበታል ማለት ነው።

የሰብአዊ መብቶች ክፍል 3 በመንግስት ባለስልጣናት ውስጥ የሚሰሩ ሁሉም ሰራተኞች ሁሉንም ህጎች፣ ፖሊሲዎች እና መመሪያዎች ሰብአዊ መብቶችን በሚያከብር መልኩ (በተቻለ መጠን) መተግበር አለባቸው ይላል።


በዕለት ተዕለት ሁኔታዎች ውስጥ እነዚህ ግዴታዎች በጣም አስፈላጊ ናቸው ምክንያቱም የሚከተሉትን ማድረግ ያስችሉዎታል፦

- ሁሉም ሰው ሰብአዊ መብቶች ስላሉት ድምጽን ከፍ አድርገው መናገር።
- ሰብአዊ መብቶችን የማክበር እና የመጠበቅ ህጋዊ ግዴታቸውን እየተወጡ ስለመሆናቸው አገልግሎቶች አቅራቢዎችን ማናገር።
- ፍርድ ቤት መሄድ ሳያስፈልግ ወይም ጠበቃ ሳይጠቀሙ የተሻሉ መፍትሄዎችን ለማግኘት ከአገልግሎቶች አቅራቢዎች ጋር መስራት።

**ከህዝብ አገልግሎቶች ወይም ህዝባዊ ተግባራቶችን ከሚሰጡ አገልግሎቶች ሰጪዎች ጋር በተገናኘን በማንኛውም ጊዜ የሰብአዊ መብቶች ህግን መጠቀም እንችላለን። ለምሳሌ፣ የHome Office፣ NHS፣ የአካባቢ ባለስልጣናት ወይም የህዝብ አገልግሎትን ውሳኔ በሚቃወም ደብዳቤዎች ላይ።**

# በሰብአዊ መብቶች ኣዋጅ ውስጥ ምን መብቶች አሉ?

በሰብአዊ መብቶች ህግ ውስጥ 16 መብቶች አሉ። ከእነዚህ መብቶች ጥቂቶቹ ፍፁም መብቶች የምንላቸው ናቸው፤ ይህ ማለት በፍፁም በህጋዊ መንገድ ሊገደቡ አይችሉም። ሌሎች ፍጹም ያልሆኑ ናቸው፤ ይህም ማለት የመንግስት ባለስልጣን የአንድን ሰው ሰብአዊ መብቶች እንዲገድብ የሚፈቀድለት አንዳንድ ሁኔታዎች አሉ ማለት ነው። እነዚህ ሁኔታዎች ልዩ ናቸው እናም አብዛኛውን ጊዜ ህጋዊ፣ እውቅና የተሰጠው እና ተመጣጣኝ ፍተሻዎችን መከተል ይኖርባቸዋል፦




አንድ የመንግስት ባለስልጣን ወይም አካል እነዚህን 3 ፍተሻዎች ማሟላት ካልቻለ ሊያደርጉት የሚፈልጉት የሰብአዊ መብቶች ገደብ ህጋዊ አይሆንም።

<u>ስለ እያንዳንዱ 16 መብቶች የበለጠ መረጃን እዚህ ማግኘት ይችላሉ።</u>

# ፍፁም እና ፍፁም ያልሆኑ መብቶች

## ፍፁም:-

- የመኖር መብት (አንቀጽ 2)
- ከስቃይ እና ኢሰብአዊ እንዲሁም አዋራጅ ከሆነ አያያዝ ነጻ የመሆን መብት (አንቀጽ 3)
- ከባርነት እና ከግዳጅ የጉልበት ሥራ ነፃ የመሆን መብት (አንቀጽ 4)
- ትክክለኛ ፍርድ የማግኘት መብት (አንቀጽ 6)
- ከሕግ ውጭ በሆነ የፈጸሙት ነገር ያለመቀጣት መብት (አንቀጽ 7)
- የአስተሳሰብ፣ የህሊና እና የሃይማኖት ነፃነት (አንቀጽ 9)
- የመማር መብት (ፕሮቶኮል 1፣ አንቀጽ 2)
- የሞት ቅጣትን መሰረዝ (ፕሮቶኮል 13፣ አንቀጽ 1)

## ፍፁም ያልሆኑ:-

- የነጻነት መብት (አንቀጽ 5)
- የግል እና የቤተሰብ ህይወት፣ የቤት እና የመልእክት ልውውጥ መብት (አንቀጽ 8)
- የአስተሳሰብ፣ የህሊና እና የሃይማኖት ነፃነት (አንቀጽ 9)
- ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት (አንቀጽ 10)
- የመሰብሰብ እና ማህበር የመፍጠር መብት (አንቀጽ 11)
- የማግባት እና ቤተሰብ የመመስረት መብት (አንቀጽ 12)
- ከአድልዎ ነፃ የመሆን መብት (አንቀጽ 14)
- በንብረት በሰላም የመዝናናት መብት (ፕሮቶኮል 1፣ አንቀጽ 1)
- የመማር መብት (ፕሮቶኮል 1, አንቀጽ 2)
- የነጻ ምርጫ መብት (ፕሮቶኮል 1፣ አንቀጽ 3)

*አንዳንድ መብቶች ሁለቱም ፍጹምም ፍፁም ያልሆኑም ናቸው። ይህ ማለት በፍፁም ሊገደብ የማይችል ክፍል አላቸው ነገር ግን በተወሰነ ሁኔታ ሊገደብ የሚችልም ክፍል ይይዛሉ ማለት ነው።

# አንቀፅ 3፦ ከኢሰብአዊ እንዲሁም አዋራጅ ከሆነ አያያዝ ነጻ የመሆን መብት

በአንቀፅ 3 ስር ያለው ከኢሰብአዊ እንዲሁም አዋራጅ ከሆነ አያያዝ ነጻ የመሆን መብት ሰዎችን ከባድ አእምሮዋዊም ሆነ አካላዊ ጉዳት በሚያደርስ ወይም በሚያዋርድ መልኩ ከመያዝ ይጠብቃል። ይህ አያያዝ፦



በጣም እንዲፈሩ ወይም እንዲጨነቁ ያደርጎታል



ከፍተኛ ህመም ያስከትልብዎታል



ዋጋ ቢስ ወይም ተስፋ ቢስ የሆኑ ያህል እንዲሰማዎ ያደርጋል

እርስዎን ከኢሰብአዊ ወይም አዋራጅ አያያዝ ለመጠበቅ የሰብአዊ መብቶች ህግን ለመጠቀም፣ አያያዙ በጣም ከባድ መሆን አለበት።

**፲ይህ መብት ፍጹም ነው። ይህም ማለት አንድ ሰው በሕዝብ ባለሥልጣን ሆነ ተብሎም ይሁን አይሁን (ወይም “ሕዝባዊ ተግባር” በሚፈጽም አካል) ኢሰብአዊ እና አዋራጅ በሆነ መንገድ መስተናገድ ፈጽሞ ሕጋዊ አይደለም ማለት ነው።**

## የጉዳይ ጥናት፦ የሎላ ታሪክ

ሎላ ጥገኝነት የተከለከለች ነፍሰ ጡር ሴት ነበረች። ትኖር የነበረው መንግስት ባዘጋጀው መጠለያ ውስጥ ሲሆን ሆስፒታል ውስጥ በምትወልድበት ወቅት 'የድጋፍ ማቆም' ማስታወቂያ ተሰጣት። ነጠላ ወላጅ ነበረች፣ እናም ይህ ሁለተኛ ልጇ ነበር።

እሷ ሆስፒታል ውስጥ እያለች ነበር የማስታወቅያው ቀነ ገደብ ያለቀው እናም ወደ ቤት ሲመለሱ እሷ እና ልጆቿ መኖሪያቸውን መልቀቅ ነበረባቸው። ሎላ ለመኖሪያ ቤት አቅራቢው በነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ ቤተሰቡን ማፈናቀል ኢሰብአዊ እና አዋራጅ በሆነ መልኩ ያለመስተናገድ መብትን ሊጥስ እንደሚችል ከገለጸው በአካባቢው ከሚገኝ የበጎ አድራጎት ድርጅት የተወሰነ ድጋፍ አገኘች (አንቀጽ 3)። የበጎ አድራጎት ድርጅቱ በሰብአዊ መብቶች ህግ መሰረት ያለባቸውን ግዴታ በመግለጽ ሎላ ተገቢ የሆነ ቤት እንድታገኝ ተጨማሪ ጊዜ እንዲኖራት የማስታወቅያው ግዜ እንዲራዘም በመጠየቅ ለቤቶች አቅራቢው ጽፏል።

አቅራቢው የማስታወቂያውን ሁኔታ ለማሻሻል ወሰነ፣ ለሎላ እና የበጎ አድራጎቱ ለቤተሰቡ የድጋፍን ለማመልከት (ክፍል 4) ግዜ ሰጣቸው። ማመልከቻው የተሳካ ነበር እናም ለቤተሰቡ መኖሪያ ቤት ተመቻቸ።

<u>ስለዚህ መብት እዚህ ጋር የበለጠ ማግኘት ይችላሉ።</u>

# አንቀጽ 8፡- የግል እና የቤተሰብ ህይወት፣ የቤት እና የመልእክት ልውውጥ መብት

የግል እና የቤተሰብ ህይወት፣ የቤት እና የመልእክት ልውውጥ መብት በሰብአዊ መብቶች ህግ አንቀፅ 8 የተጠበቀ ነው። የዚህ መብት እያንዳንዱ ክፍል ብዙ የተለያዩ ነገሮችን ይከላከላል።

**የግል ሕይወት መብት የሚከላከለው፡-**

- ደህንነት (የአእምሮ ወይም የአካል ጤና)
- ራስን በራስ ማስተዳደር (ሰዎችን በራሳቸው አካል እና ህይወት ላይ በሚወስኑ ውሳኔዎች ውስጥ ማካተት)
- በማህበረሰቡ ውስጥ የሚደረግ ተሳትፎ
- ከሌሎች ጋር ያለ ግንኙነትዎች
- ሚስጥራዊነት

**የቤተሰብ ሕይወት መብት የሚከላከለው፡-**

- መደበኛ የቤተሰብ ግንኙነቶችን ማዳበር
- የተለያዩ ከሆነ ቀጣይነት ያለው ግንኙነት

**በቤት ወስጥ መብት የሚከላከለው፡-**

- አሁን ባልዎ ቤትዎ መደሰት። ይህ መኖሪያ ቤት የማግኘት መብት አይደለም ነገር ግን አሁን ባለዎት ቤት ደስተኛ መሆንን ያስከብራል። ለምሳሌ፣ ይህ መብት ያለ እርስዎ ፈቃድ ፖሊስ ወይም ሌላ የህዝብ አገልግሎት ወደ ቤትዎ ከመግባት ይከላከላል።

**የመልእክት ልውውጥ መብት የሚከላከለው፡-**

- ከሌሎች ጋር ክትትል የማይደረግበት ግንኙነት ማድረግ
- ደብዳቤዎች እና ዘመናዊ ግንኙነቶች (ፅሁፎች፣ ኢሜይሎች፣ የስልክ ጥሪዎች)

ይህ መብት ፍፁም ያልሆነ ነው፣ ይህም ማለት ማንኛውም የዚህ መብት ገደብ ህጋዊ፣ እውቅና የተሰጠው እና ተመጣጣኝ ፍተሻዎችን ማሟላት አለበት።

ህጋዊ፦ የመንግስት ባለስልጣናት ያንን እርምጃ ወይም ውሳኔ እንዲወስዱ የሚፈቅድ ህግ አለ.

እውቅና የተሰጠው፦ ጥሩ ምክንያት አለ (ለምሳሌ የህዝብ ደህንነት ወይም የሌሎች ሰዎችን መብት መጠበቅ)

የተመጣጠነ፦ ስለሌሎች ሊያደርጉ የሚችሉ ነገርዎች አስበዋል፣ ነገር ግን የሚመለከተውን ሰው ወይም ሌሎች ሰዎችን ለመጠበቅ ሌላ መንገድ የለም። ካሉት የመጨረሻው የገደብ አማራጭ መሆን አለበት።

## የጉዳይ ጥናት፡ የሆማ ታሪክ

ሆማ በደቡብ ለንደን ነው የሚኖረው። በአገሩ የደረሰበትን ስቃይ ተከትሎ ወደ እንግሊዝ ከሸሸ በኋላ፣ ጥገኝነት የመጠየቅ ሂደት ላይ ነበር። ሆማ ያመለጠበት አደጋ ከአሰቃቂ ክስተት በኋላ በሚመጣ (post-traumatic) የጭንቀት እክል እንዲታወክ አድርጎታል እናም ወደ ህክምና ቀጠሮው እንዲሁም ሌሎች የድጋፍ አገልግሎቶች ለመድረስ ወደ ሰሜን ለንደን መጓዝ ነበረበት። ሆማ በመጠባበቅ ላይ ስላለው የጥገኝነት ማመልከቻ እና ስደት እንዲሁም እንግልት ሊደርስበት በሚችልበት ወደ ትውልድ ሀገሩ ሊመለስ ስለሚችል በጣም ተጨንቆ ነበር።

ከአሰቃቂ ክስተት በኋላ በሚመጣ የጭንቀት እክሉ ምክንያት ሆማ ከ10 ደቂቃ በላይ በአውቶቡስ ውስጥ በሚቆይበት ቦታ ሁሉ የፍርሃት ስሜት ያጋጥመዋል። ከአውቶቡሱ በመውርድ ራሱን አረጋግቶ የሚቀጥለውን አውቶቡስ መጠበቅ ይኖርበት ነበር። አንዳንድ ጊዜ ወደሚፈለገው ቦታ ለመድረስ ብዙ ሰአታት ይወስድበታል፣ እናም ከተሰጠው ውስን ገንዘብ ላይ ብዙውን እየተጠቀመ ነበር ምክንያቱም ብዙ ጊዜ ለብዙ የአውቶቡስ ጉዞዎች መክፈል ነበረበት። የሆማ ጉዳይ ሰራተኛ ሊን ረጅሙ ጉዞ ከነበረበት የአእምሮ ጤና ሁኔታ ጋር ተዳምሮ በደህንነቱ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ እያሳደረ መሆኑን ተረዳ።

ሊን በተለየ መልኩ ለተቸገሩ ሰዎች የአውቶቡስ ማለፍያ የማቅረብ ኃላፊነት ለነበረው ለአካባቢው ምክር ቤት ጽፎ የሆማ የግል ሕይወትን የማክበር መብት (አንቀጽ 8) እና በተለይም ይህ የሰዎችን የስነ-ልቦና ታማኝነት መብት እንዴት እንደሚጠብቅ ተናገረ። የአካባቢው ምክር ቤት ሁኔታው በሆማ ደህንነት ላይ ያሳደረው ከፍተኛ ተጽእኖ የግል ህይወቱን የማክበር መብት ላይ ጣልቃ እየገባ መሆኑን እና ይህን ተጽእኖ ለመቀነስ ተመጣጣኝ እርምጃ የመውሰድ ግዴታ እንዳለባቸው ተስማሙ። ሆማ በራሱ ፍጥነት ወደ ቀጠሮው እንዲሄድ እና የሚፈልገውን ህክምና እንዲያገኝ የአውቶቡስ ማለፊያ ተሰጠው።

<u>ስለዚህ መብት እዚህ ጋር የበለጠ ማግኘት ይችላሉ።</u>

# አንቀጽ 14፦ ከአድልዎ ነፃ የመሆን መብት

ይህ ከአድልዎ ነፃ የመሆን ራሱን የቻለ መብት አይደለም። በሰብአዊ መብቶች ህግ ውስጥ ባሉ ሌሎች መብቶችዎ ላይ በሚታመኑበት ወቅት አድልዎ ያለመድረስ መብት ነው። ከአድልዎ ነፃ የመሆን መብት አንዳንድ ጊዜ 'በጀርባ የሚታዘል' መብት ተብሎ ይጠራል። ይህ ማለት ከሌሎቹ መብቶችዎ አንዱ አደጋ ላይ በሚሆንበት ጊዜ፣ ችግር እንዳለው ካሰቡ ከአድልዎ ነፃ የመሆን መብትዎን ማንሳት ይችላሉ።

## የሰብአዊ መብቶች ኣዋጅ እና የእኩልነት ኣዋጅ

የሰብአዊ መብቶች ኣዋጅ፣ እንደ የእኩልነት ኣዋጅ ካሉ ሌሎች የአድሎ ህጎች በተለየ መልኩ ክፍት ነው። ይህም ማለት ከሌሎች ሕጎች በተለየ መልኩ ሰፋ ባሉ ሁኔታዎች ላይ ሊተገበር ይችላል። የእኩልነት ኣዋጅ መድልዎን የሚከለክለው በ9 የተጠበቁ ማንነትዎች የሚባሉ ምክንያቶች ነው። እነዚህም፦ ዕድሜ፣ አካል ጉዳተኝነት፣ የጾታ ዳግም ድልድል፣ ጋብቻ እና የሲቪል አጋርነት፣ እርግዝና እና እናትነት፣ ዘር፣ ሃይማኖት ወይም እምነት፣ ወሲብ እና ወሲባዊ ዝንባሌ ናቸው።

የሰብአዊ መብቶች ሕግ የጾታ፣ ዘር፣ ቀለም፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖትን፣ ፖለቲካዊ ወይም ሌሎች አመለካከት፣ ብሄራዊ ወይም ማህበራዊ መነሻ፣ ከአናሳ ብሔረሰብ ጋር ግንኙነት ማድረግ፣ ንብረት ወይም ውልደት የመሳሰሉ ምክንያቶች ዝርዝር በማስቀመት እርስዎ ላይ የሚደረግን አድሎ ህገ-ወጥ ያደርገዋል። ከዚያም በኋላ "ወይም ሌላ ሁኔታ" ስለሚል መጨረሻው ክፍት ነው፣ የህግ ዳኛዎች ጾታ፣ ማንነት፣ ወሲባዊ ዝንባሌ፣ ጤና እና አካል ጉዳተኝነት፣ የወላጅነት እና የጋብቻ ሁኔታ እንዲሁም የስደት ሁኔታ እንደሚያካትት ወስነዋል። ይህ በጥምር ምክንያቶች አድልዎ መድረስንም ሊያካትት ይችላል - ልክ እንደ ወጣት፣ ጥቁር፣ አካል ጉዳተኛ መሆን። የሰብአዊ መብቶች ህግ የመንግስት አካላት ላይ ይህንን መብት የማክበር እና የማስጠበቅ ህጋዊ ግዴታን የሚጥል ሲሆን የእኩልነት ህጉ ግን ሱቆች እና ሬስቶራንቶችን ጨምሮ የመንግስት እና የግል አካላትን ይመለከታል።

ይህ መብት ማለት የሰብአዊ መብቶች ህግን በሚጠቀሙበት ጊዜ ልክ እንደ ማንኛውም ሰው መታየት ይኖርብዎታል ማለት ነው። ይህ ማለት፦

- በዘርህ፣ በእድሜ፣ በሀይማኖት፣ በፆታ ማንነት፣ በስደት ሁኔታዎ ወዘተ ምክንያት በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ካሉ ሌሎች ሰዎች በባሰ መስተንግዶ አለመስተናገድ።
- ከሌሎች በተለየ ሁኔታ ውስጥ በሚሆኑበት ወቅት በተለየ ሁኔታ ያለመስተናገድ፣ ለምሳሌ አስተርጓሚ በጣም በስፈለግዎት ጊዜአለመስጠት።

## የጉዳይ ጥናት፦ የሴሊን ታሪክ

ሴሊን በEssex ውስጥ ትኖር የነበረች ሲሆን ጥገኝነትም አጊንታ ነበር። ለተወሰኑ ሳምንታት ወደ ሆስፒታል መሄድ ነበረባት።

ሴሊን ለተወሰነ ጊዜ እንግሊዝኛ ስትማር ነበር፣ ነገር ግን ቋንቋውን ስትጠቀም ምቾት አይሰማትም ነበር፣ በተለይም ደግሞ ሃኪሞች የተወሳሰቡ ቃላቶችን በሚጠቀሙበት ወቅት። ዶክተሩ ያደረገችውም በርካታ ምርመራዎች ውጤት ለመስጠት መጣች። ሴሊን የነገራት ነገር በትክክል አልገባትም ነበር። አስተርጓሚ ጠየቀች ነገር ግን እንግሊዝኛዋ በቂ እንደነበር እና እንደማያስፈልጋት ተነገራት።

የሴሊን ጓደኛ በሆስፒታል ውስጥ አገኘቻት እና ሰብአዊ መብቶቿን መጠቀም እንደምትችል ነገረቻት። ሴሊን ያለ አስተርጓሚ ህክምናዋን በትክክል መረዳት እና ማውራት ባለመቻሏ ይህ የሴሊን ደህንነት እና ራስን በራስ የማስተዳደር መብት (የግል እና የቤተሰብ ህይወት መብት አካል) ላይ ተጽእኖ እያሳደረ መሆኑን እና ይሄ መድሎ መሆኑን ለሆስፒታሉ ሰራተኞች ነገሩዋቸው። ሰራተኞቹ እጅግ በጣም አስፈላጊ በሚሆንበት ወቅት ብቻ አስተርጓሚ እንዲጠቀሙ የሚያዘውን የሆስፒታሉን ፖሊሲ መከተላቸውን ገለጹ፣ ምክንያቱም ሆስፒታሉን ብዙ ወጪ ስለምያሶጣው።

ይህ ፖሊሲ በሰብአዊ መብቶች ህግ አንቀጽ 8 ስር ያለውን የሆስፒታሉን ግዴታ የማይወጣ እና እንግሊዘኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆኑ ሰዎች አንቀጽ 14'ን በሚጥስ መልኩ ፍትሃዊ ያልሆነ አድሎ እንዲደርስባቸው እንደሚያደርግ የምያብራራ ደብዳቤ የሴሊን ጓደኛ ለሆስፒታሉ ታካሚ አማካሪ እና ግንኙነት አገልግሎት እንድትጽፍ ረዳቻት።

ሆስፒታሉ ተስማምቶ ፖሊሲውን በመቀየር እንግሊዘኛ የመጀመርያ ቋንቋቸው ላልሆነ ሰዎች ሁልጊዜ ተርጓሚ እንዲዘጋጅ ተደርጓል።

<u>ስለዚህ መብት እዚህ ጋር የበለጠ ማግኘት ይችላሉ።</u>

# ሰብአዊ መብቶች በሙግት፡- ደብዳቤ አጻጻፍ

የሰብአዊ መብቶችን ቋንቋ ተጠቅመው ጉዳዩን ለሚመለከተው የመንግስት አካል ካነሱ እና ጉዳዩን መደበኛ ባልሆነ መንገድ መፍታት ካልቻሉ ደብዳቤ መጻፍን ማሰብ ይኖርብዎታል።

ይህ ብዙ ጥቅሞች አሉት፣ በተለይም ድርጅቱ በምላሹ ደብዳቤ ሊጽፍልዎት ስለሚችል። ደብዳቤ ሁኔታውን ለማብራራት፣ የተፈለገውን ውጤት ለመለየት እና ሁኔታውን ለመመዝገብ የሚያስችል መንገድ ይሰጥዎታል።

## ደብዳቤ ለመጻፍ ጠቃሚ ምክሮች

- እውነታውን ያስቀምጡ። ሁኔታውን ለማብራራት በቂ ዝርዝር መስጠት አለቦት ነገር ግን የሚጽፉላቸውን ሰዎች ግራ እንዳይገባቸው በጣምም ማብዛት የለብዎትም። ከ 1 ገጽ ያልበለጠ ያድርጉት።
- የትኛውን መብት ሊከላከሉ ወይም ሊያከብሩ እንዳልቻሉ ለይተው ይግለጹ። ለምን እንደዛ እንዳሰቡ ይንገሯቸው።
- ምን ማድረግ ነበረባቸው እንዲሁም አሁን ምን ማድረግ አለባቸው ብለው የሚያስቡትን ያብራሩ።
- ግልጽ፣ ጨዋ ይሁኑ እና መልስ እንደሚጠብቁ ያመልክቱ።
- ጉዳይዎን ለማያውቅ ሰው ትርጉም ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ ሌላ ሰው እንዲያነበው ያድርጉት።

# 1) የግለሰብ ምሳሌያዊ ደብዳቤ

የእርስዎ ስም
25 Example Street
L17UX
የእውቂያ ኢሜይል/ቁጥር

ለምን እየጻፉላቸው እንዳለ እንዲያውቁ ማን እንደሆኑ እና ከምክር ቤቱ ጋር ያልዎትን ግንኙነት ያስረዱ።

የተከበሩ Mrs Bloggs,

ስሜ Ms X ይባላል እናም የምኖረው በ25 Example Street, L17UX, የአካባቢው ባለስልጣን ንብረት ውስጥ ነው1። እየጻፍኩ ያለሁት በውጪኛው በር ጋር ካለው መብራት ጋር ስለተያያዘ ቀጣይነት ያለው ችግር ነው። መብራቱ ለ3 ወራት ተበላሽቶ ቆይቷል ይህም ማለት በማረፊያው በኩል ወደ በሩ መሄድ አለብኝ እናም በሬን በጨለማ ውስጥ መክፈት አለብኝ። ይህ ከባድ ጭንቀት እየፈጠረብኝ ነው እናም ከጨለማ በኋላ ቤቴን ለቆ መውጣትም ሆነ ወይም መመለስ ያስፈራኛል። ይህ በተለይ በክረምት ወራት በህይወቴ ላይ ትልቅ ተጽእኖ እያሳደረ ይገኛል። ይህንን ጉዳይ ለቤቶች ኦፊሰሬ ብዙ ጊዜ አንስቼው ነበር እናም ይህ በአእምሮ ጤንነቴ ላይ የሚያሳድረውን ተጽእኖ፣ ድንጋጤን ጭምር ገልጬ ነበር። በተለይም እኔ ከቶርቸር የዳንኩ በመሆኔ ተፅዕኖው ከፍተኛ እንደነበርም ገልጫለሁ። ይሁን እንጂ መብራቱ አሁን ድረስ አልተስተካከለም።

ዳራውን እና ምን እንደተከሰተ ያብራሩ። በእርስዎ ላይ እያደረሰ ያለውን ተጽእኖ ያሳውቁ።

እንደ የአካባቢው አስተዳደር የመኖሪያ ቤትዎች መምርያ በሰብአዊ መብቶች ህግ መሰረት መብቶቼን የማክበር እና የማስጠበቅ ህጋዊ ግዴታ አለባቹ።3 የመብራቱ ጉዳይ ለተወሰኑ ወራት የቀጠለ በመሆኑ እና ድንጋጤን ጨምሮ በአእምሮ ጤንነቴ ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ እያሳደረ በመሆኑ፣ ይህ ኢሰብአዊ እና አዋራጅ የመስተንግዶን ደረጃ ላይ ሊደርስ ይችላል (በሰብአዊ መብቶች ህግ ላይ አንቀጽ 3 ) በተለይም ከቶርቸር የተረፍኩ መሆኔን ግምት ውስጥ በማስገባት። በዚህ ጉዳይ ላይ እርምጃ አለመወሰዱ በአካልና በአእምሮ ጤንነቴ ላይ ጣልቃ እየገባ ይገኛል ይህም የግል እና የቤተሰብ ህይወትን የማክበር መብቴ የተጠበቀ ነው (አንቀጽ 8) ከአማካሪዬ ዶ/ር ጃኮብስ በአዕምሮ ጤንነቴ ላይ ያለውን ተጽእኖ የሚገልጽ ደብዳቤ አያይዤአለሁ።

በሰብአዊ መብቶች ህግ መሰረት ግዴታ እንዳለባቸው ያስረዱ።

የትኞቹ መብቶች ተጥሰዋል ብለው እንደሚያስቡ እና ለምን እንደሆነ ያብራሩ። በመጀመሪያ ፍፁም በሆኑ መብቶች ላይ ያተኩሩ፣ ከዚያም ፍፁም ያልሆኑትን። ይህ በተለየ ሁኔታ በእርስዎ ላይ ያለውን ተጽእኖ ለማሳየት፣ ለመግለጽ ምቾት የሚሰማዎትን የግል ዝርዝሮችን ማከል ይችላሉ። ለምሳሌ:- ይህ ከአእምሮ ጤናዎ፣ ከቀደምትዎ ልምድ ወይም ከቤተሰብዎ ሁኔታ ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል። እንዲሁም የእርስዎን ጉዳይ የሚደግፍ ማንኛውንም አይነት ማስረጃ ማለትም እንደ ከዶክተሮች ወይም ከድጋፍ ሰራተኞች የተቀበሉትን ደብዳቤዎች ማቅረብ ይችላሉ።

የሰብአዊ መብቶች ህግ ማለት ማንኛውም የፍፁም መብት ገደብ ለምሳሌ እንደ ከኢሰብአዊ እና አዋራጅ መስተንግዶ ነጻ የመሆን መብት ፈጽሞ ህጋዊ አይደለም ማለት ነው። ስለሆነም ወደ ቤት ስመለስ ደህንነት እንደሚሰማኝ እና ከአሁን በኋላ ኢሰብአዊ እና አዋራጅ አያያዝ አደጋ ላይ እንዳልወድቅ መብራቱን ለማስተካከል ወዲያውኑ እርምጃ መወሰድ አለበት። እንደ የግል እና የቤተሰብ ህይወት መብት ስር ያለ ጤናማ የመሆን መብትን የመሰለ ፍጹም ያልሆነ መብት ገደብ ህጋዊ፣ እውቅና ያለው እና ተመጣጣኝ መሆን አለበት። ከቤቴ ውጭ ያለውን መብራት ላለማስተካከል የተደረገው ውሳኔ እውቅና አለው ነው ብዬ አላምንም፤ ይህንን መብት ለመገደብ በቂ ምክንያት የለም፣ ለምሳሌ የህዝብ ደህንነት ወይም የሌሎች ሰዎችን መብት መጠበቅ። ይህ ሁኔታ በእኔ እና በመብቴ ላይ እያሳደረ ያለውን ተጽእኖ ከግምት ውስጥ በማስገባት መብራቱ እንዲስተካከልልኝ ከ3 ወር በላይ መጠበቅ ለእኔ ተመጣጣኝ አይደለም። ስለዚህ፣ ከቤቴ ውጭ ያለው መብራት እንደ አስቸኳይ ጉዳይ ታይቶ እንዲስተካከልልኝ እጠይቃለሁ።

ይህንን ችግር ለመፍታት ምን እንዲደረግ እንደሚፈልጉ ያብራሩ።

ከላይ ካለው ቀን ጀምሮ በሚቀጥሉት ሁለት ሳምንታት ውስጥ ለደብዳቤዬ ምላሽ ቢሰጡኝ ምስጋናዬ የላቀ ነው6፣ ይህንን ችግር በሰላማዊ መንገድ መፍታት እንደምንችል እርግጠኛ ነኝ።

ለቀጣይ እርምጃዎች ተስማሚ የሆነ የጊዜ ገደብን ያውጡ።

ከአክብሮት ጋር
የእርስዎ ስም

# 2) የግለሰብ ምሳሌያዊ ደብዳቤ/ኢሜል

ለምን እየጻፉላቸው እንዳለ እንዲያውቁ ማንነትዎን እና ከቤቶች ቡድን ጋር ያልዎትን ግንኙነት ያስረዱ።

የተከበሩ Mrs Smith

ስሜ Ms. Y ይባላል እናም የምኖረው 25 Example Street, L17UX7 በጥገኞች ማረፍያ ውስጥ ነው። ማርች 17፣ 2022 ወደ ሌላ ቦታ እንደምዘዋወር እና አዲሱ አድራሻዬ በአገሪቱ ውስጥ ባለ በማንኛውም ቦታ ሊሆን እንደሚችል የሚገልጽ የደረሰኝን ደብዳቤ ተከትሎ ነው ይህንን እየጻፍኩ ያለሁት። ይህ ትልቅ ጭንቀት ፈጥሮብኛል። በፆታዊ ዝንባሌዬ ምክንያት ተሰድጄ ጥገኝነት ጠያቂ ሆኜ እንግሊዝ ከገባው በኋላ አሁን ባለሁበት ከተማ ለ2 ዓመታት ኖሪያለሁ። የአካባቢያዊ LGBT የድጋፍ ቡድን ንቁ አባል መሆንን ጨምሮ ለአእምሮዬ እና ለስሜታዊ ጤንነቴ አስፈላጊ የሆነ ሰፊ የድጋፍ መረብን ገንብቻለው እዚህ። በተጨማሪም እሷ ከአካባቢው ከራቀች ሊቋረጥ የሚችል የባለሙያ የህክምና አገልግሎት እየተሰጠኝ ነው.

ዳራውን እና ምን እንደተከሰተ ያብራሩ። በአንተ ላይ እያደረሰ ያለውን ተጽእኖ ያሳውቁ።

ልዩ ሁኔታዎች ከሌሉ በስተቀር የማረፍያ ፖሊሲያቹ በአጠቃላይ ያለ ምርጫ እንደሚሰጥ እረዳለው። የHome Office የማረፍያ ድልድል ፖሊሲ እያንዳንዱን ጥያቄ እንደየሁኔታው እንዲያጤኑት ይጠይቃል እናም “በአንድ የተወሰነ ቦታ ላይ ማረፍያ ቦታን ላለማመቻቸት ከተወሰነ ምክንያቶች መሰጠት አለባቸው እንዲሁም ውሳኔው በሰብአዊ መብቶች ህግ መሰረት የHome Office ግዴታዎች ጋር መጣጣም አለባቸው” (p5)።

ከተቻለ ጉዳይዎን የሚደግፍ ፖሊሲ ወይም ህጎችን ያጣቅሱ። ሕጎች በተቻለ መጠን ሁሉ ሰብዓዊ መብቶችን በሚደግፉ መልኩ መተርጎም እንዳለባቸው ይጠቁሙ።

በHome Office ስር የተዋዋለው የመኖሪያ ቤት አቅራቢ እንደመሆኖንዎ፣ መብቶቼን ለማክበር እና ለመጠበቅ በሰብአዊ መብቶች ህግ መሰረት ያለውን ህጋዊ ግዴታ ማክበር አለባችሁ።

በሰብአዊ መብቶች ህግ መሰረት ግዴታ እንዳለባቸው ያስረዱ። ምንም እንኳን የቤቶች ማህበር የግል ኩባንያ ቢሆኑም እንኳን በHome Office (የህዝብ አካል) ስር የተዋዋሉ በመሆኑ የሰብአዊ መብቶች ህግ ግዴታ ይሰራል።

የሕክምና እንክብካቤዬን ማቋረጥ በአካላዊ እና በአእምሮ ጤንነቴ ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ይኖረዋል፣ ይህም ኢሰብአዊ እና አዋራጅ የሆነ አያያዝ ደረጃ ላይ ሊደርስ ይችላል (በሰብአዊ መብቶች ህግ አንቀጽ 3 የተከለከለ)፣ በተለይም የሚደረግልኝ እንክብካቤ ልዩ ባለሙያ የሚፈልግ መሆኑን ስናስብ። አካላዊ፣ አእምሯዊ እና ስሜታዊ ደህንነቴም በግል እና በቤተሰብ ህይወቴ መብት የተጠበቀ ነው (አንቀጽ 8)። ከድጋፍ ስርአቴ እና የLGBT ማህበረሰብ ቡድኔ እኔን ማራቅ በግል ህይወቴ መብት ላይ ጣልቃ ይገባል፣ በተለይም ከዚህ ቀደም በፆታዊ ዝንባሌዬ መክንያት ስቃይ ገጥሞኝ ስለነበር። ከማህበረሰቡ ቡድን መሪ ስለሰጡኝ ድጋፍ የሚገልጽ ደብዳቤ አያይዤያለሁ።

Eየትኞቹ መብቶች ተጥሰዋል ብለው እንደሚያስቡ እና ለምን እንደሆነ ያብራሩ። በመጀመሪያ ፍፁም በሆኑ መብቶች ላይ ያተኩሩ፣ ከዚያም ፍፁም ያልሆኑትን። ይህ በተለየ ሁኔታ በእርስዎ ላይ ያለውን ተጽእኖ ለማሳየት፣ ለመግለጽ ምቾት የሚሰማዎትን የግል ዝርዝሮችን ማከል ይችላሉ። ለምሳሌ:- ይህ ከአእምሮ ጤናዎ፣ ከቀደምትዎ ልምድ ወይም ከቤተሰብዎ ሁኔታ ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል። እንዲሁም የእርስዎን ጉዳይ የሚደግፍ ማንኛውንም አይነት ማስረጃ ማለትም እንደ ከዶክተሮች ወይም ከድጋፍ ሰራተኞች የተቀበሉትን ደብዳቤዎች ማቅረብ ይችላሉ።

የሰብአዊ መብቶች ህግ ማለት ማንኛውም ፍፁም የሆነ መብት ገደብ፣ ለምሳሌ ኢሰብአዊ እና አዋራጅ ከሆነ አያያዝ ነጻ የመሆን መብት በፍፁም ህጋዊ አይደለም ማለት ነው። ስለዚህ፣ ይህ ተገቢውን የህክምና አገልግሎት እንዳላገኝ የሚያስተጓጉልኝ ወይም የሚከለክልኝ ወደሆነ አዲስ አካባቢ መወሰድ የለብኝም። የግል እና የቤተሰብ ህይወት መብትን የመሳሰሉ ፍፁም ያልሆኑ የመብት ገደቦች ህጋዊ፣ እውቅና ያላቸው እና ተመጣጣኝ መሆን ይኖርባቸዋል። እኔን ካለሁቤት ቦታ ለማስቀየር የተወሰነው ውሳኔ እውቅና የለውም ብዬ አምናለው፣ እኔን ለማዘዋወር በቂ ምክንያት ስለሌለ። ሌሎች አማራጮችን እንዳሰባቹ ስላላሳያቹኝ ተመጣጣኝ ነው ብዬም አላምንም። ስለዚህ እኔን የማዛወር ዕቅዱ እንደ አስቸኳይ ጉዳይ ታይቶ እንዲሰረዝ እጠይቃለሁ።

ይህንን ችግር ለመፍታት ምን እንዲደረግ እንደሚፈልጉ ያብራሩ።.

የቦታ ዝውውሩ በቅርቡ ጊዜ የተያዘለት በመሆኑ፣ ለደብዳቤዬ ምላሽ ማርች 15፣ 2022 4pm ላይ ቢሰጡኝ ምስጋናዬ ከፍ ያለ ይሆናል።

ለቀጣይ እርምጃዎች ተስማሚ የሆነ የጊዜ ገደብን ያውጡ።

ከአክብሮት ጋር
የእርስዎ ስም

## ምላሽ ከተቀበሉ ቀጥሎ ምን ማድረግ እንዳለብዎት

Iምላሹ ጠቃሚ ከሆነ እና የህዝብ ባለስልጣኑ ሁኔታውን ለመፍታት እንዴት መርዳት እንደሚችሉ ከእርስዎ ጋር ለመወያየት ከፈለገ ከእርሱ ጋር ለመገናኘት እና በጉዳዩ ላይ የበለጠ ለመወያየት ይጠይቁት። ይህ ስብሰባ የግድ በአካል መሆን አይጠበቅበትም፣ በስልክም ሊሆን ይችላል፦

- እናደርጋለን የሚሉትን ማንኛውንም ነገር ጨምሮ በስብሰባዎቹ ላይ ጥሩ ማስታወሻ መያዝዎን አይዘንጉ።
- የሚተገበርበትን ጊዜ ይጠይቁ እና ማስታወሻ ላይ ያስቀምጡት።
- የጠየቁትን እርማቶች ካልተገበሩ ወይም በተስማሙበት የጊዜ ገደብ ውስጥ ይህን ካላደረጉ፣ እንደገና ከእነሱ ጋር ለመገናኘት ይጠይቁ። ቅሬታዎ በፍጥነት ካልተመለሰ ከፍ ወዳለ ቦታ እንደሚወስዱት ይንገሯቸው።
- Iእርስዎ ደስተኛ ካልሆኑ እና እነርሱ ቅሬታዎን በቁም ነገር ሊመለከቱት ካልቻሉ ወይም መብቶችዎን ችላ ማለታቸውን ከቀጠሉ ዋናውን የጥያቄ ቀን እና ይዘት በመጥቀስ ሌላ ጥያቄ ማቅረብ ይኖርብዎታል።

## ምላሽ ካላገኙ ቀጥሎ ምን ማድረግ እንዳለብዎት

እንደ ጉዳይዎ ክብደት እና አጣዳፊነት፣ በተመጣጣኝ ጊዜ ውስጥ ምንም አይነት ምላሽ ካላገኙ ደብዳቤዎ መድረሱን ለማረጋገጥ በስልክ መከታተል አለቦት።

ደብዳቤው ካልደረሰ፦

- በድጋሚ ይላኩት እና በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ምላሽ እንዲሰጡ ጥብቅ ጥያቄ ያቅርቡ።
- ደብዳቤው እንደደረሳቸው የሚገልጽ ማረጋገጫ እንደሚፈልጉ ይንገሯቸው።

ደብዳቤው ደርሶዋቸው ከሆነ ነገር ግን የሚመለከተው ግለሰብ መቼ ምላሽ እንደሚሰጥ ግልጽ ካላደረገ ወይም ጉዳዩን በቁም ነገር ካልተመለከተው፦

- የደብዳቤዎን ግልባጭ ለህዝብ ባለስልጣን አስተዳደር (ለምሳሌ ዋና ስራ አስፈፃሚ ወይም በምክር ቤት ውስጥ ያለ የአገልግሎት ኃላፊ) ይላኩ።
- ስለቀደመው ደብዳቤዎ ይግለጹ እንዲሁም የተላከበትን ቀን እና ለማን እንደተላከ ያካትቱ።
- ለመጀመሪያ ደብዳቤዎ ምንም አይነት ምላሽ እንዳላገኙ ለአስተዳዳሪው/ዋና ሥራ አስፈፃሚ/ለአገልግሎት ኃላፊው ይንገሩ።
- የመጀመሪያውን ደብዳቤ ለተቀበለው ሰው የወሰዱትን እርምጃ ለመንገር ተጨማሪ ደብዳቤ መላክም ይችላሉ። ይህ በፍጥነት እርምጃ እንዲወስዱ ሊያበረታታቸው ይችላል።

# ሰብአዊ መብቶች በሙግት፡- ምላሽዎን ከፍ ማድረግ

ጣልቃ-ገብነትዎን ከፍ ማድረግ ብዙ መንገዶችን ሊወስድ ይችላል፦

- የሰብአዊ መብቶች ክርክሮችን በተከታይ ደብዳቤዎች ማጠናከር።
- ስለ መልሱ ለመወያየት አፋጣኝ ስብሰባ ለማድረግ መጠየቅ
- ችግሩ ካልተፈታ የበለጠ ከባድ እርምጃ ለመውሰድ እንደሚገደዱ ማስጠንቀቅ።
- በቀጥታ ወደ ከፍ ያለው ደረጃ አስተዳደር መጻፍ።
- ምላሽ ካላገኙ እና ለህዝብ ባለስልጣናት አቤቱታ አቅርበው ችግሩ ካልተፈታ፣ ወደ እንባ ጠባቂ መሄድ ይችላሉ። ይህ የእርስዎን ችግር ማየት የሚችል ራሱን የቻለ ግለሰብ ነው። ቅሬታ ባሰሙበት አገልግሎት ላይ በመመስረት የተለያዩ እንባ ጠባቂዎች አሉ። ስለ እንባ ጠባቂዎች የበለጠ እዚህ ማንበብ ይችላሉ።
- ሁኔታው ካልተፈታ፣ የህግ አማካሪ መጠየቅ ሊኖርቦት ይችላል። አንዳንድ የህግ ማማከር አገልግሎቶች በነጻ ሊሰጡ ይችላል። ለነጻ የህግ ማማከር አገልግሎት ብቁ መሆንዎን እዚህ ማወቅ ይችላሉ።
- የቅድመ ድርጊት ፕሮቶኮል ደብዳቤ ለመጻፍ ጠበቃ ሊረዳዎ ይችላል። ይህ የፍርድ ቤት ሂደት ከመጀመሩ በፊት አለመግባባቶችን ለመፍታት ይረዳል። ብዙውን ጊዜ፣ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ምንም አይነት ምላሽ ካልተገኘ፣ የፍርድ ቤት ሂደት ይጀምራል። ስለዚህ ወደ ፍርድ ቤት መሄድ ካለበት የቅድመ እርምጃ ፕሮቶኮል ደብዳቤን ከመላክዎ በፊት የሕግ ምክር ማግኘት ጠቃሚ ነው።

እርስዎ የሚወስዱት አካሄድ ምናልባት በጉዳዩ አጣዳፊነት እና ትምህርት ቤቱን/የአካባቢው አስተዳደር/ሆስፒታሉን ወይም ጉዳዩ በተነሳበት ሌላ አካልን ላለማራቅ የሚሰማዎት ጭንቀት ላይ ይወሰናል። በአንፃራዊነት ከግጭት የጸዳ አካሄድ መፍትሄ ሊያመጣ ይችላል ብለው ካመኑ እና የህዝብ ባለስልጣኑ ለጥያቄዎችዎ ምላሽ ለመስጠት ጥረት እያደረገ እንደሆነ ካመኑ፣ ግለሰቦቹን በቀጥታ ለማነጋገር ስብሰባን መጠየቁ (በተጨማሪ) ጠቃሚ ይሆናል።

## ስለ ውሳኔያቸው ማብራሪያን መጠየቅ

ማንኛውም የክትትል ደብዳቤ ወይም ስብሰባ እርስዎን ያሳሰቦትን ውሳኔ ለመወሰን እንዴት እንደደረሱ እንዲገልጹ ባለስልጣኑን መጠየቅ አለበት። ይህንን በመጠየቅ ብዙውን ጊዜ ጉዳዩን ከህግ አንፃር እንዲመለከቱት ያስገድዷቸዋል። ይህ ብዙውን ጊዜ ወደ አጥጋቢ ምላሽ እንዲሰጡ ሊመራቸው ይችላል።

እንዲሁም ውሳኔውን ለመቃወም ከድጋፍ ሰጪ ቡድኖች ወይም አማካሪዎች እርዳታ መፈለግን ቀላል ስለሚያደርግ ተጨማሪ እርምጃ ከመውሰድዎ በፊት ሙሉ ምክንያታቸውን ማግኘቱ ጠቃሚ ነው።

## የሰብአዊ መብቶች ክርክሮችን ማጠናከር

### የበለጠ ዝርዝር ያቅርቡ

የሰብአዊ መብቶች ጉዳይ ለምን እንደሆነ በዝርዝር ያስረዱ። ይህ ምናልባት በግለሰቡ ላይ የሚደርሰውን ስቃይ መጠን በበለጠ ዝርዝር መግለጽ እና ተዛማጅ አንቀጾችን ይዞት መጥቀስን ይጨምራል።

### በተመጣጣነ መልኩ መፍታት

ባለሥልጣኑ የተወሰነ የሰብአዊ መብቶች ገደቦች እንደነበሩ ሊቀበል ይችላል፣ ነገር ግን አቀራረባቸው ሌሎች ሊያሟሏቸው የሚገቡትን ጥያቄዎች ግምት ውስጥ በማስገባት ተመጣጣኝ ምላሽ እንደሆነ ያምናል።

ወደዚህ ውሳኔ እንዴት እንደመጡ ይጠይቋቸው እናም ለምን ተመጣጣኝ አይደለም ብለው እንደምያስቡ በዝርዝር ይግለጹላቸው – ለምሳሌ፦ ሌላ አቀራረብን በመጠቆም ወይም የሚመለከተውን ግለሰብ ስቃይ መጠን በመግለጽ።

### ፍጹም የሆኑ መብቶች ጥሰት

ጥሰቱ ኢ–ሰብአዊነት እና አዋራጅ የሆነ አያያዝን ወይም ለህይወት አስጊ ነው ብለው ካመኑ፣ 'የተመጣጠነ' ምላሽ አጥጋቢ አይሆንም። ፍፁም የሆነው መብትዎ ለምን ተጥሷል ብለው እንደምያምኑ ለባለስልጣኑ ይንገሩ። እንደዚህ አይነት መብቶች በየትኛውም ሁኔታ የማይፈቅዱ መሆናቸውን እና ባለስልጣኑ ተጨማሪ ጉዳት እንዳይደርስ ለመከላከል እንዲሁም ሁኔታውን ለማስተካከል በአስቸኳይ እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው ያስታውሱ።

# ሰብአዊ መብቶች በሙግት፡- መዝግቦ ማስቀመጥ

ከህዝብ ባለስልጣን ጋር ያለዎትን ግንኙነት ለመመዝገብ ሊጠቀሙበት የሚችሉት ሰንጠረዥ ይኸውሎት። ተጨማሪ እርምጃዎችን መውሰድ ከፈለጉ ይህ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። የመጀመሪያው መስመር እንደ ምሳሌነት ተሞልቷል።

| ቀን | ማንን ነበር ያነጋገሩት? | እንዴት አነጋገሯቸው? | ምን አሉ? |
|---|---|---|---|
| 08/04/2022 | የቤቶች አስተዳዳሪ | ስልክ | ፍሳሹን የሚያስተካክል ሰው ነገ ይልካል። |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |

Created as part of the BIHR Co-Design A Human Rights Support Solution Project
Published April 2022

ይህ ሰነድ ለመረጃነት አገልግሎት ብቻ ነው። እንደ የህግ ምክር ወይም መመሪያነት የታሰበ አይደለም፣ እንደዛ ጥቅም ላይ መዋልም የለበትም። በዚህ ሰነድ ውስጥ የተጠቀሰው ህግ ከታተመበት ጊዜ በኋላ ተለውጦ ሊሆን ይችላል።